# ስለ Medicaid እና CHIP የበለጠ እንዲያውቁ አስፈላጊ መረጃ

Medicaid እና የልጆች ጤና መድህን ፕሮግራም(CHIP) ነጻ ወይም ዝቅተኛ የጤና መድህን ፕሮግራም ለእርስዎና ለቤተሰብዎ ማቅረብ ይችላል። ለ Medicaid እና CHIP ሽፋን ማመልከት ደህንነቱ የተጠበቀ ነው።

ቤተሰብዎ ስደተኛ የሆኑ ግለሰቦችን ካካተተ፣ ማወቅ ያለብዎት አስፈላጊ መረጃ እነሆ፡

- የስቴት Medicaid እና CHIP ኤጀንሲዎች ለጤና ሽፋኑ ላመለከተው ግለሰብ ብቻ የሚያስፈልገውን መረጃ ይሰበስባል፣ ይጠቀማል፣ እንዲሁም ይፋ ያደርጋል።
- ለሽፋን ካላመለከቱ የቤተሰብ አባላትዎ ጋር የዜግነት ወይም የስደተኝነት ሁኔታ መረጃን በፍጹም ማጋራት የለብዎትም። በእርስዎ ማመልከቻ ላይ፣ ለሽፋን ያላመለከቱ የቤተሰብ አባላትዎን “አመልካች ያልሆኑ” በሚል ይለዩዋቸዋል።
- Medicaid እና CHIP የእርስዎን እና የቤተሰብዎን መረጃ በሚስጥር ለመጠበቅ፣ ጠንካራ የሆነ የግላዊነት ከለላዎችን ተግብሯል። ለሽፋን የእርስዎን ቤተሰብ እየረዳ ያለ ግለሰብ የእርስዎን ቤተሰብ ግላዊነት ለመጠበቅ ጥብቅ የሆኑ ደንቦችን መከተል ይገባዋል። እነዚህ ግለሰቦች የሚያካትቱት የ Medicaid እና CHIP ሰራተኞችን፣ አሳሾችን፣ የተመሰከረላቸው የማምለከቻ አማካሪዎችን፣ ኤጀንቶችን፣ ደላሎችን እና የስልክ ጥሪ ማእከል ተወካዮችን ነው።
- በአጠቃላይ፣ ለ Medicaid እና CHIP ጥቅማጥቅሞች ማመልከት ወይም ማግኘት፣ ወይም በገበያ ስፍራ ለጤና መድህን ወጪዎች ቁጠባዎችን መግኘት፣ በ ”ህዝባዊ ክፍያ” ሙከራ ውስጥ አይቆጠርም። የአንድ ግለሰብ ህጋዊ ቋሚ ነዋሪ የመሆን እድሉ ላይ ተጽእኖ አያደርግም። ለዜግነት፣ ህዝባዊ የክፍያ ሙከራ የለም።
  - የነርሲንግ ቤት አይነት ባለ በመንግስት ወጪ የሚሸፈን ተቋም ውስጥ፣ የረዥም ጊዜ እንክብካቤ ለሚያገኙ ሰዎች አንድ የማይካተት ነገር አለ። እነዚህ ሰዎች ግሪን ካርድ ለማግኘት መሰናክሎች ሊገጥሟቸው ይችላል።
  - በህዝባዊ ክፍያ ውሳኔ ላይ ለአጭር ጊዜያት መልሶ ማቋቋም ተቋማዊነት ከግምት ውስጥ አይገባም።
  - የ CHIP ጥቅማጥቅሞች በህዝባዊ ክፍያ ውሳኔ ውስጥ በምንም አይነት ሁኔታ ከግምት ውስጥ አይገቡም።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ በ **1-877-KIDS-NOW (1-877-543-7669)** ላይ ይደወሉ ወይም **“ለቤተሰብዎ ሽፋንን ያግኙ”** የሚለውን ክፍል በ **InsureKidsNow.gov** ላይ ይጎብኙ። እርስዎ ወይም ከቤተሰብዎ አንድ ሰው እንግሊዝኛ መናገር፣ ማንበብ፣ መጻፍ፣ ወይም መረዳት የማይችል ከሆነ፣ ነጻ የቋንቋ ድጋፍ አለ።

InsureKidsNow.gov



Paid for by the U.S. Department of Health & Human Services

CMS Product No. 12127-AMH
January 2022